# በ24ኛው አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ የሚሻሻሉ የመመስረቻ ፅሁፍ አንቀጾች፡-

I. በ22ኛው አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ የኩባንያው ካፒታል እንዲያድግ በተወሰነው መሰረት አሁን ላይ የኩባንያው የተፈረመ እና የተከፈለ ካፒታል ወደ ብር 1,680,142,000 (አንድ ቢሊዮን ስድስት መቶ ሰማንያ ሚሊዮን አንድ መቶ አርባ ሁለት ሺ ብር) ያደገ እና የባለአክስዮኖች ቁጥር ወደ 99 ከፍ ያለ በመሆኑ የተሻሻለው መመስረቻ ጽሁፍ አንቀጽ 3 እንደሚከተለው ይሻሻላል፡-

**አንቀጽ ሶስት**

**የባለአክሲዮኖች ዝርዝር መግለጫ**

የማህበሩ ባለአክሲዮኖች ስም ዝርዝር፣ አድራሻ፣ ዜግነት፣ የያዙት የአክስዮን ብዛት፣ የከፈሉት የገንዘብ መጠን እንደሚከተለው ነው፡- (ዝረዝር ሰንጠረዥ ይገባል)

II. የኩባንያውን የተፈረመ እና የተከፈለ የካፒታል መጠን የሚያሳየው ከዚህ በፊት የነበረው የመመስረቻ ፅሁፍ አንቀፅ አምስት ሥር የነበሩት ሶስት ንዑስ አንቀጾች ሁለት ተደርገው ያደገውን ካፒታል መሰረት በማድረግ እንደሚከተለው ይሻሻላል፡-

**አንቀጽ አምስት፡**

**የማህበሩ ዋና ገንዘብ /ካፒታል/፤**

5.1. የማህበሩ የተፈረመ እና የተከፈለ ዋና ገንዘብ /ካፒታል/ ብር 1,680,142,000 (አንድ ቢሊዮን ስድስት መቶ ሰማንያ ሚሊዮን አንድ መቶ አርባ ሁለት ሺ ብር) ነው፡፡

5.2. የተፈረመ እና የተከፈለ የማህበሩ ዋና ገንዘብ እያንዳንዳቸው ብር 1,000.00 (አንድ ሺ ብር) ዋጋ ባላቸው 1,680,142 (አንድ ሚሊዮን ስድስት መቶ ሰማኒያ ሺ አንድ መቶ አርባ ሁለት ሺ) በሆኑ መደበኛና የተመዘገቡ አክሲዮኖች የተከፋፈለ ነው፡፡

III. ኩባንያው በ23ኛው አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ የመመስረቻ ፅሁፍን እና የመተዳደሪያ ደንቡን አጠቃሎ አንድ የመመስረቻ ፅሁፍ አጽድቋል፡፡ ምንም እንኳን የካፒታል ገበያ አዋጅ ቁጥር 1248/2013 አስቀድሞ የወጣ ቢሆንም፤ ከዚህ ጉባዔ በኋላ የኢትዮጵያ ሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ ባለስልጣን በሕዝብ የተያዙ እና ከ50 በላይ ባለአክስዮኖች ያላቸው ኩባንያዎች አክስዮኖቻቸውን እንዲያስመዘግቡ አስገዳጅ የሆነውን የመመሪያ ቁጥር 1030/2017ን አውጥቷል፡፡ በሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ ዙሪያ ኩባንያው የሚኖረውን ተሳትፎ ለመወሰን

የንግድ ዓላማውን ጭምር በጊዜ ሂደት ማሻሻል ቢገባም፤ አሁን ላይ የመድን ሥራን የሚደነግገው አዋጅ ቁጥር 746/2004 ያልተለወጠ እና ማሻሻያ ያልተደረገበት በመሆኑ የሚቻል አይደለም፡፡ ሆኖም የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ ባለስልጣን ካወጣቸው መመሪያዎች እና ኩባንያው በነዚህ መመሪያዎች ምክንያት የሚጣሉበትን ግዴታዎች ያለችግር መወጣት እንዲችል የመመስረቻ ጽሁፉ አንቀጾች መጠነኛ ማሻሻያ የሚስፈልጋቸው ይሆናል፡፡

በካፒታል ገበያ አዋጅ ቁጥር 1248/2013 እና ይህንን ተከትሎ በወጣው ለሕዝብ የሚሸጡ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ግዑዝ አልባ የማድረግ መመሪያ ቁጥር 1047/2017 አክስዮኖች ግዑዝ አልባ ሆነው በማዕከላዊ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ግምጃ ቤት መረጃ እንዲያዝ ስለሚያስገድድ የባለአክስዮኖች መዝገብ አያያዝን በተመለከተ በማዕከላዊ የሰነዶች ግምጃ ቤት ስለሚቀመጡበት ሁኔታ በመመስረቻ ፅሁፉ ላይ በግልጽ ማስቀመጥ ያስፈልጋል፡፡

**ማሻሻያ፡-**

የመመስረቻ ጽሁፉ አንቀጽ 11 ስለባለአክስዮኖች መዝገብ የነበረው ድንጋጌ ተሽሮ በሚከተለው መልኩ ተተክቷል፡-

**አንቀጽ አሥራ-አንድ**

**ስለ አክስዮን መዝገብ አያያዝ እና አክስዮኖችን ግዑዝ አልባ ስለማድረግ**

11.1. አክስዮን ማሕበሩ የባለአክስዮኖችን መዝገብ፣ አክስዮኖችን እና አክስዮኖችን የሚመለከቱ መረጃዎችን በንግድ ህግ አዋጅ ቁጥር 1243/2013 አንቀጽ 272 እና 274፣ በሰነደ ሙዓለ ንዋይ አዋጅ ቁጥር 1248/2013 እና ይህን ተከትለው በወጡ መመሪያዎች መሰረት ግዑዝ አልባ በሆነ ኤሌክትሮኒክስ እንዲመዘገቡ እና እንዲያዙ ያደርጋል፤

11.2. አክስዮን ማሕበሩ የባለአክስዮኖችን መዝገብ በኤሌክትሮኒክ ዘዴ ያደራጃል፣ በማዕከላዊ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ግምጃ ቤት ያስመዘግባል፣ በማዕከላዊ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ግምጃ ቤት ጋር በመተባበር ወቅታዊ መረጃዎችን ያዘምናል፤

11.3. ከዚህ በፊት በወረቀት የወጡ አክስዮኖች በግዑዝ አልባ አክስዮኖች እንዲተኩ ይደረጋል፤

11.4. ከላይ የተቀመጠው እንደተጠበቀ ሆኖ አክስዮን ማሕበሩ በህግ ወይም በመመስረቻ ጽሁፍ የተመለከቱ ዝርዝሮችን የያዘ የራሱን የውስጥ መዝገብ ወይም ላወጣቸው አክሲዮኖች ምስለ መዝገብ ለመያዝ ይችላል፤

11.5. የባለአክስዮኖች መረጃ ትክክለኛ ስለመሆኑ ከማዕከላዊ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ግምጃ ቤት ጋር በትብብር ይሰራል፤ ሥህተት ካለ ይመረምራል፤ እንዲስተካከል ያደርጋል፡፡

IV. የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ ባለስልጣኑ ባወጣቸው መመሪያዎች እና በሚያራምደው ፖሊሲ ዋና ፍላጎቱ ኩባንያዎች አክስዮኖችን በአክስዮን ገበያ በግልጽነት እንዲገበያዩ ማድረግ ነው፡፡ በዚህም የአክስዮን ዝውውርን የሚገድቡ የመመስረቻ ጽሁፍ ድንጋጌዎች ተቀባይነት አይኖራቸውም፡፡ በመሆኑም አክስዮኖች ያለገደብ እንዲዘዋወሩ ለማስቻል በአክስዮን ሽያጭ ላይ ያሉ የቀደምትነት መብቶች እና ገደቦች ከመመስረቻ ፅሁፉ እንዲወጡ ማድረግ አስፈላጊ ይሆናል፡፡

**ማሻሻያ፡-**

የመመስረቻ ጽሁፉ አንቀጽ 12 (2)" እና 12 (3)" እንደሚከተለው ይሻሻላል፡-

12.2. አክስዮኖች ከአንድ ሰው ወደ ሌላ ሰው ያለምንም ገደብ ይተላለፋሉ፡፡"

12.3. የአክስዮን ዝውውርን እና ማስተላለፍ ሂደትን በተመለከተ አግባብነት ያላቸው የካፒታል ገበያ ህጎች እና መመሪያዎች ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል፡፡"

V. በ23ኛው አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ፣ ዓመታዊ ጠቅላላ ጉባኤ የሚደረግበት ጊዜ የበጀት ዓመቱ ባለቀ በአራት (4) ወር ውስጥ የሚል ድንጋጌ በባለአክስዮኖች ጥያቄ መሰረት በመመስረቻ ጽሁፉ ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ ተካቷል፡፡ ሆኖም የኢንሹራንስ ኩባንያዎች ዓመታዊ የሂሳብ ሪፖርቶች በገለልተኛ ኦዲተር ለማረጋገጥ ብቻ ሳይሆን በአጠቃላይ የሚሰሩት ሂሳቦች በአክቹአሪስ ተሰርተው መቅረብ ስለሚጠበቅባቸው ልክ ዘንድሮ ያጋጠሙንን ችግሮች ከግምት በማስገባት ለቀጣይም ቢሆን በአራት(4) ወር ጊዜ ውስጥ ዓመታዊ ጠቅላላ ጉባኤ መጥራት የማይቻልባቸው ሁኔታዎች ቢኖሩ ተጨማሪ መጠባበቂያ የሁለት(2) ወር ጊዜ በመመስረቻ ጽሁፍ ለማስቀመጥ ስለሚቻል ዓመታዊ ጠቅላላ ጉባኤ የመጥሪያ ጊዜውን ከአራት(4) ወደ ስድስት(6) ወር ማራዘሙ አስፈላጊ ነው፡፡

**የመመስረቻ ጽሁፉ አንቀጽ 14 (2) እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡-**

"14.2. መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ፣ የበጀት ዓመቱ በተዘጋ በስድስት(6) ወራት ውስጥ በዓመት አንድ(1) ጊዜ መደረግ አለበት፤ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ተጨማሪ መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔዎች ሊደረጉ ይችላሉ፡፡"